በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ከግጭት ጋር በተያያዘ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች አካታችነት ማሳደግን አስመልክቶ የተዘጋጀ የፖሊሲ መግለጫ

Policy Brief on Promoting Inclusivity of Conflict Related Sexual Violence Survivors in the Ethiopian Transitional Justice Process

Association for Human Rights in Ethiopia (AHRE)

With funds from

Consortium of Ethiopian Human Rights Organizations (CEHRO)

© ASSOCIATION FOR HUMAN RIGHTS IN ETHIOPIA
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
SEPTEMBER 2024

DISCLAIMER
THE FUNDER OF THIS PUBLICATION CANNOT BE RESPONSIBLE FOR ANY FACTUAL OR LEGAL ERRORS OR OMISSIONS IN THIS PUBLICATION.

ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ

ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃና እድገት የተቋቋመ፣ መንግስታዊ ያልሆነ፣ ከወገንተኝነት የፀዳ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። ድርጅታችን በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት ሁኔታዎችን ለማሻሻል ጥልቅ ምርምር በማድረግ፣ ለሰብአዊ መብቶች ተሟጋች በመሆን እና በሰብአዊ መብቶች ላይ ስልጠና በመስጠት ለመብቶች መረጋገጥ ትልቅ ሚና የሚጫወት እንዲሁም በአገሪቱ ያለውን የሰብአዊ መብት ሁኔታ የማሻሻል ጥረት ላይ መንግስትን እና የሚመለከታቸውን አካላትን መደገፍ አላማው ያደረገ ድርጅት ነው። ድርጅቱ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፱፲3/20፲፩ መሰረት በምዝገባ ቁጥር 5223 የተመዘገበ ነው።።

ሀ. መግቢያ

በግጭት፣ በመፈናቀል እና መሰል ወቅቶች ህጻናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አዛውንቶች ከፍተኛ አደጋ ላይ ይወድቃሉ። ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች በተጨማሪ ወጣት ልጃገረዶች እና ሴቶች ከፍተኛ ለሆነ ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት ተጋላጭ ናቸው። በትግራይ ክልል ግጭት ከተቀሰቀሰበት ግዜ አንስቶ የአለም አቀፍ የሰብአዊ ህግጋቶች እና የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግጋት ጥሰቶች በሰፊው ተፈጽመዋል። በጦርነት ውስጥ የተሳተፉ ሁሉም ወገኖች በሚባል ደረጃ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶችን፣ የሰብአዊነት እና የስደተኞች መብቶች ላይ የህግ ጥሰቶችን የፈጸሙ ሲሆን አንዳንዶቹም የጦር ወንጀል እና በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሊሆኑ ይችላሉ።[1]

የ2019 የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እንደሚያትተው "ጥቃቶች ከስርዓተ ጾታ ምልከታ ጋር የተቆራኙ ከመሆናቸው አንፃር የወንጀል ምርመራዎች እና ሀገራዊ እና ከባቢያዊ ሂደቶች ለእውነት እና ዕርቅ በተለይ ለጾታዊ እና ጾታ-ተኮር ጥቃቶች እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲፈጸሙ እያስቻሉ ያሉ የፆታ ልዩነትን የሚያሰፉ ሁነቶች ላይ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል።"

የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ለረጅም ጊዜ ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ፣የህግ የበላይነት፣ ፍትህ እና ዴሞክራሲን ተግባራዊ ለማድረግ መሳሪያ እንደሆነ ይታመናል። በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ ሲሆን ፖሊሲው የወንጀል ምርመራና ክስ፣ እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር፣ በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት፣ ማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያ ማዕቀፎችን ያስቀመጠ ነው። ፖሊሲው ተጎጂዎችን እና የወንጀለኞችን የቃላት ፍቺን ከመስጠት ባለፈ ከጥቃት ወይም ከጉዳት መጠበቅ፣ አካታችነትና አሳታፊነት፣ ስርዓተ-ጾታ ተኮር አተገባበርን እንደ መርህ የያዘ እና ተጎጂዎችን ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።

የሽግግር ፍትህን ጨምሮ በተለያዩ ሂደቶች ውስጥ ከግጭት ጋር በተያያዘ የፆታ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎችን (conflict related sexual violence survivors) ማካተት ካለው ወሳኝ ጠቀሜታ አንጻር እና የተደራጁ የውትወታ ጥረቶች አለመኖራቸውን በመገንዘብ፣ ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ(AHRE) ይህንን ክፍተት መሙላት አላማ ያደረጉ ተግባራትን አቅዶ እየሰራ ቆይቶአል። እቅዱም ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ፣ የውትወታ ስልቶችን በመጠቀም፣ እና የፖሊሲ

[1] [1] Global centre for responsibility to protect, June 1, 2022, available at https://www.globalr2p.0rg.ethiopia

መግለጫን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ማጋራት፣ ከግጭት ጋር በተያያዘ የፆታ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎችን ትርጉም ባለው እና በተሻለ መልኩ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ በማካተት፣ ለፍትህ ተደራሽነት አስተዋጽኦ ማድረግ፣ ማገገም እና አጠቃላይ ደህንነት ማረጋገጥን ያለመ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ይህን የፖሊሲ መግለጫ ማዘጋጀት አስፈላጓል፡፡

ለ. የፖሊሲ መግለጫው ዓላማ

ከመጋቢት 2015ዓ.ም ጀመሮ በፍትህ ሚኒስቴር በኩል የተቋቋመዉ የባለሙያዎች የስራ ቡድን (የስራ ቡድን) ከባለሙያዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እና ከሲቪክ ማህበራት ከተውጣጡ አካላት ጋር ህዝባዊ ምክክር በማድረግ ግብዓቶችን እና አስተያየቶችን ሰብስቧል፣ ይህም አገር አቀፍ ባለቤትነት ያለው ሁሉንም ያካተተ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እንዲሆን ያስችላል። ሆኖም ይህ ሁሉን አቀፍ አሳታፊነት በትግበራው ሂደትም መቀጠል ያለበትና ሊበረታታ የሚገባ ተግባር ሲሆን ከግጭት ጋር በተያያዘ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎችን ጉዳይ ከግንዛቤ ያስገባ እና አካታች መሆን ይኖርበታል፡፡
ፖሊሲው ለመቅረፅ እንዲሁም ወደ ፊት ለማምጣት የተደረገው ከፍተኛ ጥረት እንዳለ ሆኖ ፖሊሲው ሁሉን አካታች በተለይም ከግጭት ጋር በተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን ያካተተ እንዲሆንና በትግበራ ወቅትም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ (ስሰመኢ) ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት(ኢሰመድህ) ጋር በመተባበር ከባለድርሻ አካላት ማለትም ፆታዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴቶች፣ በአማራ ክልል (ደሴ) የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ማዕከል(one stop centers)፣ በከተማው ከሚገኙ ሴቶች ላይ የሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፤ የሴቶችና የወጣት ማህበራት ተወካዮችን እና የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ጋር፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከሚመለከታቸው የመንግስት እና በሴቶች እና በሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ውይይት በማድረግ የሽግግር የፍትህ ሂደቱ ከግጭት ጋር በተያያዘ የፆታ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎችን አካታችነት ለማሳደግ ይረዳሉ ተብለው የተነሱ ሃሳቦችን ለመሰብሰብ ችሏል። የዚህ ሰነድ ዓላማም እነዚህን አካታችነትን በተሻለ ሁኔታ ለማረጋገጥ ይረዳሉ የተባሉ ነጥቦችን ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡

ሐ. የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ

1. ሴራሊዮን

ሴራሊዮን ለ11 ዓመታት የዘለቀ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ የነበረች ሀገር ስትሆን ተዋጊ ወገኖች በጦርነቱ ወቅት ጾታዊ ጥቃት ሽብር ለመፍጠር እንደ እኩይ ስልት ይጠቀሙ ስለነበር ድርጊቱ በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሰፋ ጉዳት ያደረሰ ነበር። ከ215,000 እስከ 257,000 የሚደርሱ የሴራሊዮን ሴቶች እና ልጃገረዶች ለጾታዊ ጥቃት ተዳርገው ሊሆን ይችላል ተብሎም ይታሰባል። ዓለም አቀፍ እና ሃገራዊ ተዋናዮች እንዲሁም የሀገሪቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሰላሙ ሂደት እና የሴራሊዮን የሽግግር የፍትህ ላይ ተሳትፈዋል። የእውነት እርቅ ኮሚሽን እንዲሁም ለሽግግር ፍትህ የተቋቋመው ልዩ ፍርድ ቤት በጋር በመሆን በአንድ ላይ የሚሰሩበት እና የስርዓተ-ፆታ ወንጀሎችን እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ልዩ ልዩ ስቃዮችን

ለመፍታት የሚያስችል ልዩ ጥረት አድርገዋል። የእውነት ኮሚሽኑ በፆታዊ ጥቃት ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት በወርሃዊ ክፍያ፣ በህክምና እና በስነ-ልቦናዊ አገልግሎቶች እንዲሁም በገንዘብ ካሳ በቀጥታ ለመፍታት ምክረ ሃሳቦችን ሰጥቷል።[2]

በሽግግር ፍትህ ሂደቱ እና በሴራሊዮን የተደረጉት ስራዎች እንደ ከግጭት በኋላ ማገገሚያ፣ ሰላም ማስከበር እና የሰላም ግንባታ ሴራሊዮንን ስኬታማ ከሆኑ ሽግግር ፍትህ ሂደቶች ካከናወኑ ሃገራት ውስጥ ምሳሌ ያደርጋታል።

2. ደቡብ አፍሪካ

የደቡብ አፍሪካ የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን (TRC) የተቋቋመው የብሔራዊ አንድነት እና እርቅ ህግን በማፅደቅ ነው። የዚህ ተቋም ስልጣን ከመጋቢት 1952ዓ.ም እስከ ግንቦት 1986ዓ.ም ኔልሰን ማንዴላ ፕሬዝዳንት ሆነው እስከተመረጡበት ወቅት ያለውን በአፓርታይድ ስርዓት የተፈጸሙትን ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መመርመር ነበር። ኮሚሽኑ በኬፕ ታውን(Cape Town)፣ ደርባን(Derban) እና ጆሃንስ በርግ(Johannesburg) ልዩ የሴቶች ችሎቶች አደራጅቶ የነበር ሲሆን እነዚህ ችሎቶች ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥሰቶችን፣ ጾታዊ ጥቃትን እና መዋቅራዊ ጥቃቶችን አጉልተው አሳይተዋል።
ኮሚሽኑም ለተጎጂዎች የገንዘብ ክፍያ፣ ካሳ፣ ተቋማዊ ማሻሻያ እና የማህበረሰብ ማቋቋሚያ ፕሮግራሞችን እንዲተገበሩ ምክረ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑ ከተጎጂዎች ጋር እየሰሩ የነበሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አገልግሎታቸውን በኮሚሽኑ እውቅና ለተሰጣቸው ተጎጂዎች እንዲያቀርቡ ሐሳብ አቅርቧል። ክሊኒኮች እና ሌሎች አገልግሎቶች ወንጀለኞችን መልሶ የማቋቋም ስራ ላይ እንዲሳተፉ መክሯል።[3]

መ. በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የደረሰባቸውን ተጎጂዎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማረጋገጥ ይረዳሉ የተባሉ ነጥቦች ይዘት

ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ባካሄዳቸው የምክክር መድረኮች ላይ የተነሱትን ጠቃሚ ያልናቸውን ምልከታዎች እና ምክረ ሀሳቦችን እንደሚከተለው አቅርበናል። የሽግግር የፍትህ ፖሊሲው በአምዶች የተቀረፀ እንደመሆኑ ምልከታዎቹን እና ምክረ ሀሳቦቹን በእነዚህ አምዶች የተከፋፈሉ ናቸው።

1. የወንጀል ተጠያቂነት

- ተጎጂዎች ያለፉበት ሁኔታ እና ያጋጠማቸው ነገር በሕይወታቸው ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳሳደረ ግምት ውስጥ በማስገባት ያለምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ እና የጾታ ልዩነት ሳይኖር የሁሉም ተጎጂ ፍትህ የማግኘት መብት መረጋገጥ አለበት።

[2] Jemma Blachlaw, African Transitional Justice Hub A CSVR Initiative, **Sierra Leone Truth and Reconciliation Commission (2002-2004), November 1, 2023 Available at "https://atjhub.csvr.org.za/sierra-leone-truth-and-reconciliation-commission-2002-2004/ "**

[3] Sinqobile Makhathini, African Transitional Justice Hub A CSVR Initiative, **Sierra Leone Truth and Reconciliation Commission (2002-2004), November 1, 2023 Available at https://atjhub.csvr.org.za/south-africa-truth-and-reconciliation-commission-1996-2002/**

- የፍትህ ስርዓቱ ተደራሽ እና ለተጎጂዎች ምቹ መሆን አለበት
- ለተጎጂዎች ህጋዊ ከለላ ሊደረግላቸው ይገባል
- ተጎጂዎች ወንጀለኞችን በመለየት እና ለህግ በማቅረብ ሂደት ላይ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ማግኘት አለባቸው በተለይ በጥሰቱ ውስጥ የተሳተፉት ወታደሮች እና ሌሎች ባለስልጣናትን የሚያካተት ሲሆን።
- ማግለል እና ኢድሎአዊ ባህሪያት የተጎጂዎችን መብቶች እንደ መጣስ ተቆጥረዉ አስተማሪ የሆነ ሀጋዊ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።
- ውጤታማ የምርመራ ሂደትን ለመደገፍ ተጎጂዎች ገላጭ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል ።
- በሽግግር ፍትህ ሥርዓቱ እና ተያያዥ ሌሎች ህጎች ዙሪያ ለተጎጂዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል።

2. እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና ዕርቅ

- "ተጎጂዎችን ማመን" ("Believe the Survivor") እንደ መርህ መያዝ አለበት። ጥቃቱን፣ ገጠመኙን በድጋሜ ማሰብ እና ማውራት በራሱ ከበቂ በላይ ከባድ መሆኑን ታሳቢ በማረግ ተጎጂዎች ታሪካቸውን እንዲሰማ እና እንዲታመን ይጠይቃሉ።
- ተጎጂዎች ድምፃቸው እንዲሰማ እና ያሳለፉት እንዲታወቅ፣ ታሪካቸው በትክክል ተመዝግቦ እውነትን በመፈለግ ሂደት ውስጥ እንዲካተት በንቃት መሳተፍ አለባቸው።
- የሴቶች ማህበራት እና ፌዴሬሽኖች እውነትን በማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና ዕርቅ ላይ እገዛ ማድረግ ይገባቸዋል። ሆኖም ግን፣ ተሳትፏቸውን በከፍተኛ ሁኔታ መገምገም እና ለሂደቱ ሚስጥራዊነት ቅድሚያ መሰጠት እንደአለበት ተጎጂዎች አሳስበዋል።
- ለተጎጂዎች ግላዊነት እና አእምሯዊ ጤንነት ሁሌም ቅድሚያ መሰጠት አለበት። በሽግግር ፍትህ ሂደቱ በየደረጃው የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍ መሰጠት ይኖርበታል።
- በሂደቱ ውስጥ የተጎጂዎችን ጓደኞች እና የቅርብ ዘመዶች በንቃት ማሳተፍ ያስፈልጋል።
- የአካባቢ የዕርቅ ዘዴዎች በቅድሚያ፣ አካታችነታቸው እና ሴቶችን ያገለሉ አለመሆናቸው መመርመር አለባቸው።
- መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን ለመፈተሽ ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው አሰራር መተግበር ያስፈልጋል።

3. ማካካሻ

- ተጎጂዎችን ያማከለ እና ሁሉንም ያካተተ መሆን አለበት፣ ማንም ተጎጂ ወደ ኋላ እንደማይቀር መረጋገጥ ይኖርበታል።
- ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና ማሕበራዊ ድጋፎች ሁሉን አቀፍ የተሃድሶ አካል መሆን አለባቸው።

የጉዳቱን ክብደት ከግምት ውስጥ በማስገባት አጠቃላይ ህክምና ሂደት መተግበር አለበት፣ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል-

- የስነልቦና ሕክምና እና የምክር አገልግሎቶችን የሚመሩ ሴት አማካሪዎችን በብዛት ማሳተፍ

- ጉዳት ላይ ያጠነጠነ የቡድን ውይይቶችን እና የልምድ ልውውጦችን ማካሄድ
- ለተጎጂዎች የሞራል ካሳ ሊኖር ይገባል

4. ተቋማዊ ማሻሻያ

- ተጎጂዎችን እንዲሁም ከተጎጊዎች ጋር የሚሰሩ ተቋማትን በማማከር ተጨማሪ ተቋማት ማቋቋም ወይም ነባሮቹ ላይ ማሻሻያ የማድረግ አስፈላጊነትን ለመለየት ጥረት ሊደረግ ይገባል ።
- ተቋማት ተደራሽ እና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆን አለባቸው።
- የሚቋቋሙና የሚሻሻሉ ተቋማት ውስጥ የሴቶች ትርጉም ያለው ውክልና እና ተሳትፎ ያስፈልጋል

ሠ. አጠቃላይ ምክረ ሀሳቦች

- በተለያዩ ክልሎች እየተከሰተ ያለው ግጭት በአስቸኳይ መቆም አለበት። በተለያዩ ቦታዎች እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶችን ለማስቆም ከመንግስት እና ሌሎች በግጭት ውስጥ እየተሳተፉ ያሉ አካላት ፖለቲካዊ ፍላጎት እና ፈቃደኝነት ሊኖር ይገባል።
- አሁንም ግጭት ያለባቸው አካባቢዎች አሉ፣ ይህ ማለት አሁንም ከግጭት ጋር የተያያዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እየተከሰቱ ነው። ስለሆነም ተጨማሪ ከግጭት ጋር የተያያዙ የፆታ ጥቃት ተጎጂዎችን(CRSV) እንዳንፈጥር መሰራት አለበት።
- አብዛኛው የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ማዕከሎች(one stop centers) ለሴቶች ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፣ ወንዶችን የማስተናግድ የሚችል እራሱን የቻለ ማዕከል መኖር አለበት።
- በሽግግር የፍትህ ሂደት ውስጥ ከግጭት ጋር በተያያዘ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ጉዳዮች ላይ ለሚሰሩ የመረጃ ሰብሳቢዎች፣ የስነዳ ሰራተኞች እና ሌሎች በጉዳዩ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለሚሳተፉ ሰዎች ስልጠና መሰጠት አለበት።
- የፍትህ ስርዓቱን እና የሽግግር የፍትህ ሂደትን በህዝብ ዘንድ እምነት እና ተቀባይነት ለመፍጠር ተጨማሪ ስራዎች መሰራት አለባቸው።
- ከግጭት በኋላ እየተባባሱ የመጡ እንደ ያለእድሜ ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ጠለፋ ያሉ ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።
- ካሳ የረጅም ጊዜ እቅድ ሲሆን የሂደቱን ውጤቶች ለማየት ደግሞ አመታትን ሊወስድ ይችላል፣ ስለሆነም እስከዚያው ድረስ ወቅታዊ እና ጊዜያዊ የሆኑ መፍትሄዎች ቢዘጋጁ።
- በተቋማት መካከል ያለው ቅንጅት ውጤታማ እንዲሆን ትኩረት መሰጠት አለበት።
- የግጭቱን ክብደት እና ጥሰት በመገንዘብ የሴቶችን እና ከግጭት ጋር በተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ተጎጂዎችን መብቶችን የሚጠብቅ አዲስ ህግ ሊወጣ ይገባል።
- ተጎጂዎች የደረሰባቸውን የጭካኔ ድርጊት መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ መንግሥት በተለይ ተጎጂዎችን የመጠበቅ ግዴታውን ባለመወጣቱ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የደረሰባቸውን ተጎጂዎች በይፋ ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባል።

About the Organization

Association for Human Rights in Ethiopia (AHRE) is a non-governmental, non-partisan, and not-for-profit organization dedicated to the advancement of human rights protection in Ethiopia through research-based investigations and evidence-based advocacy at the national level, including providing capacity building on human rights with the aim of supporting the government and other stakeholders in their effort to enhancing human rights situation in the country. The organization is registered under the FDRE Authority for Civil Society Organizations through proclamation number 1113/2019 with registration number 5223.

1. Introduction

During times of crisis and displacement children, women, persons with disability and elderly persons are at a heightened risk. In addition to all the difficulties they face, young girls and women are faced with high gender-based violence and sexual gender based violence. Since clashes erupted in the Tigray region of Ethiopia, widespread violations of International Humanitarian Law and International Human Rights Law have been committed throughout the conflict, in which all sides in the civil war had committed violations of international human rights, humanitarian and refugee law, some of which may amount to war crimes and crimes against humanity.[4]

The 2019 African Union Transitional Justice/TJ/ Policy states, "Given the gendered dimension of violence, criminal investigations and national and local processes for truth and reconciliation should give particular attention to sexual and gender-based violence as well as to patterns of gender inequality in the society that enable gender-based violence."

The Ethiopian TJ is believed to be a tool for long lasting peace, reconciliation, rule of law, justice and for democracy to be implemented. In April 2024, the long awaited Ethiopian TJ got ratification from the council of ministers. The policy aimed to put a framework for

[4] [1] Global centre for responsibility to protect, June 1, 2022, available at https://www.globalr2p.0rg.ethiopia

criminal investigation and prosecution, truth-seeking, reconciliation, conditional amnesty, compensation and institutional reform.

In light of the critical importance of including Conflict Related Sexual Violence/CRSV/ survivors in various processes including TJ and recognizing the absence of organized advocacy efforts for their inclusion, AHRE has developed and initiated a targeted intervention. The intervention plan encompasses a strategic framework, including stakeholder engagement, using advocacy strategies and policy brief to reach to pertinent stakeholders with the aim of enhancing meaningful inclusion of CRSV survivors and contributing to their access to justice, recovery and overall well-being. Therefore this policy brief is developed as part of the advocacy effort.

2. Objective of the policy brief

Starting March 2023, the working group of experts that was formed by the Ministry of Justice held public consultations with experts, political parties, and civil society organizations and was able to collect input and suggestions for an all-inclusive and a transitional policy that has a nationwide ownership. Even though, the initiative is commendable and should be incorporated in the implementation process the issues of and the inclusion of CRSV survivors in the TJ process must not be sidelined.

Similar to the effort that is made to the coming together for the formation and coming to light of the policy, similar if not more efforts are required to make the transitional justice process an all-inclusive with special consideration of victims of conflicted sexual violence survivors in consideration of the atrocity victims face.

The objective of this policy brief is to promote conflict CRSV survivors' inclusivity in the Ethiopian TJ process through survivor centered approach where survivors meaningful engagement is ensured and they are fully protected. AHRE in collaboration with Consortium of Ethiopian Human Rights Organizations (CEHRO) has conducted consultations with stakeholders including CRSV survivors, one stop centers, case managers, duty bearers and women rights CSOs located in Dessie, Amhara region as well as with key stakeholders from government, women and human right focused CSO's in Addis Ababa. From the consultation AHRE was able to gather recommendations on how

to better ensure inclusivity of the TJ in particular CRSV survivors' throughout the process. The objective of this document is therefore to avail these recommendations to stakeholders.

3. Countries experience

A. Sierra Leone

Sierra Leone's civil war lasted 11 years. Sexual violence was used as part of vicious tactics by the leaders of opposing factions to inflict terror, and it was committed disproportionately against women and girls. As many as 215,000 to 257,000 Sierra Leonean women and girls may have been subjected to sexual violence. Both international and regional actors, as well as local civil society organizations, were involved in the peace process and negotiating Sierra Leone's transitional justice architecture. The truth reconciliation commission (TRC) was established alongside the Special Court for Sierra Leone where the two mechanisms operated simultaneously and both made specific efforts to address gendered crimes. In relation to CRSV, the truth commission made recommendations to directly address the harm suffered due to sexual violence through monetary compensation in the form of monthly payments and medical treatment and psychosocial services.[5]

All of the works done through transitional justice and other interventions to sustain peace made Sierra Leone represent one of the world's most successful cases of post conflict recovery.

B. South Africa

The Truth and Reconciliation Commission (TRC) of South Africa was established through the adoption of the Promotion of National Unity and Reconciliation Act (1995). Its mandate was to investigate the gross human rights violations that occurred under apartheid between March 1960 and May 1994, when Nelson Mandela was inaugurated as president.

[5] Jemma Blachlaw, African Transitional Justice Hub A CSVR Initiative, **Sierra Leone Truth and Reconciliation Commission (2002-2004), November 1, 2023 Available at "https://atjhub.csvr.org.za/sierra-leone-truth-and-reconciliation-commission-2002-2004/ "**

The commission recommended reparations in the form of monetary payments, symbolic reparations, institutional reforms and community rehabilitation programmes. The commission recommended that nongovernmental organizations working with survivors extend their services to survivors acknowledged by the TRC. It also recommended that clinics and other appropriate services facilitate the rehabilitation of perpetrators.[6]

4. Recommendations made to help ensure meaningful participation of conflict related sexual violence survivours in the transitional justice process

AHRE has compiled and would like to present important insights and recommendations gathered through consultations held with stakeholders. As the transitional justice policy is framed with pillars we have also categorized the recommendations accordingly.

A. Investigation and Prosecution

- ➔ Considering what the survivors had gone through and what they have experienced justice needs to be served impartially, without any kind of exception.
- ➔ The justice system must be accessible and victim-friendly.
- ➔ Legal protection shall be rendered to CRSV survivors.
- ➔ Victims should receive full support in identifying and prosecuting perpetrators, especially if perpetrators are soldiers and other authorities who had taken part in the violation.
- ➔ Stigmatization and discriminatory behavior towards survivors must be condemned and treated as a violation of survivors rights and be punishable.
- ➔ Survivors should actively participate in the collection of descriptive evidence to support an effective investigation process.
- ➔ Awareness creation sessions shall be held for survivors about the legal and the TJ process

[6] Sinqobile Makhathini, African Transitional Justice Hub A CSVR Initiative, **Sierra Leone Truth and Reconciliation Commission (2002-2004), November 1, 2023 Available at** **https://atjhub.csvr.org.za/south-africa-truth-and-reconciliation-commission-1996-2002/**

B. Truth-seeking, Disclosure and Reconciliation

- ➔ "Believe the Survivor" should be a guiding principle. As reliving the violent experience is traumatic enough, survivors demand to have their stories heard and believed.
- ➔ Survivors must actively participate in the truth-seeking process to ensure their voices are heard and their experiences are acknowledged and documented properly.
- ➔ While women's associations and federations should aid in the pursuit of truth-seeking, Disclosure and Reconciliation, survivors stress the need to assess their involvement critically and prioritize confidentiality.
- ➔ Priority should always be given to the privacy and mental health of survivors. Psychosocial support should be provided at every stage of the TJ process.
- ➔ Actively involve friends and close relatives of survivors in the process, as they will be useful to assist, considering their close interaction with survivors.
- ➔ Local reconciliation methods shall be researched first to ascertain they are inclusive and do not exclude women.
- ➔ Implement a clear and accountable system for fact-checking of information and data.

C. Compensation

- ➔ The approach must be victim-centered and inclusive, ensuring that no victim is left behind.
- ➔ Economical, psychological, and social support should all be a part of holistic restitution.

Given the severity of trauma, a comprehensive trauma healing process should be implemented, including:

- ➔ Women counselors leading and facilitating the trauma healing and counseling process, public awareness campaigns on trauma healing.
- ➔ Group trauma debriefing, experience-sharing sessions.
- ➔ There should be moral compensation for survivors.

D. Institutional Reform

- ➔ In collaboration with survivors and organizations working directly with survivors, efforts shall be made to identify if more institutions shall be formed or if restructuring existing ones is needed.
- ➔ Institutions shall be accessible for people with disabilities.
- ➔ Survivors emphasized the need for meaningful representation and participation of women in institutions.

5. General recommendation

- ➔ The ongoing conflict in several regions must come to an immediate end. There needs to be a political willingness from the government and all parties to end the ongoing conflict in different places.
- ➔ There are still areas of active conflict, which means CRSV is still happening. We need to work and make sure we don't create more cases of survivors.
- ➔ Most safe houses and GBV centers are only giving service to women. There needs to be a separate center that can effectively treat men CRSV survivors.
- ➔ Training shall be given to data collectors, documentation workers and everyone that will be working in CRSV survivors cases throughout the transitional justice process.
- ➔ More work needs to be done to build trust in the judicial system and the transitional justice process in the eyes of the public.
- ➔ Issues that are escalating “post conflict” such as early marriage, FGM and abduction shall be given attention.
- ➔ Restitution and reparation is a long term plan which could take years to process and see results. As the situation of CRSV survivors is dire, a timely solution shall be in place until then.
- ➔ Collaboration and coordination between institutions shall be effective and given focus.
- ➔ New legislation should be introduced to specifically protect the rights of women and survivors of conflict-related sexual violence (CRSV), recognizing the severity of the conflict and the widespread violations.

➔ Given the level of atrocities experienced by CRSV survivors, the government must issue a public apology specifically to the survivors for failing in its obligation to protect them.

ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጲያ

AHRE

ASSOCIATION FOR HUMAN RIGHTS IN ETHIOPIA